


ሙሴ ባሪያ

QQD
892.816
SAM

254,804

SAMU'EL LAGGASA

[Welo lafar. Personal reflections in verse. Amharic text. Addis Abba, 1955 E.C., 1962-3.]

254804

ውሉሞ ፡ ላፈር



ከሣሙኤል ፡ ለገሠ ፡ ተዘጋጀ ።




አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፺፰ ዓ. ም. ይሀ ፡ መጽሐፍ ፡

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

ማስገንዘቢያ ።

በዚህ ፣ መጽሐፍ ፣ ውስጥ ፣ የተነገረውን ፣ እንደገና ፣ ለማሳተምም ፤ ለማባዛትም ፤ ለመተርጐምም ፣ ያለደራሲው ፣ ፈቃድ ፣ በሕግ ፣ ክልክል ፣ ነው ።

ደራሲው ፣ ሣሙኤል ፣ ለገሠ ።



ይህችን ፡ «ሙሉ ፡ ላፈር» ፡ ብዬ ፡ የሰየምኳትን ፡ መጽሐፌን ፡
ለአንባቢያን ፡ ከማሳተሜ ፡ በፊት ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ሐምሌ ፡ ፲፭ ፡
ቀን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንደአበረከትኩ ፡፡

፩ ፤ መቅድም ፡ ከገጽ ፡ ... . ፯
፪ ፤ መግቢያ ፡ ከገጽ ፡ .... ፱
፫ ፤ መግለጫ ፡ በገጽ፡ ....
፬ ፤ የልጅ ፡ አነጋገርና ፡ የአባት ፡ መልካም ፡ ሐሳብ ፡
ከገጽ ፡ ፲፭ ፡ እስከ ፡ ገጽ ፡ .... ፲፪
፭ ፤ ያቶ ፡ ጋሜና ፡ የወይዘሮ ፡ ነቃሽ ፡ ታሪክ ፡ ከገጽ፡
፲፫ ፤ እስከ ፡ ገጽ ፡ ... . ፲፱
፮ ፤ ያቶ ፡ እንደውነቱና ፡ የአጨሌ ፡ ታሪክ ፡ ከገጽ ፡
፲፱ ፡ እስከ ፡ ገጽ ፡ ... . ፳፮
፯ ፤ ኧረ ፡ እሜቴ ፡ እመቤቴ ፡ ከገጽ ፡ ፳፱ ፡ እስከ ፡
ገጽ ፡ .... ፴፪
፰ ፤ ሣቅህን ፡ ለነገ ፡ አድርገው ፡ የግዴለው ፡ ታሪክ ፡
ከገጽ ፡ ፴፪ ፡ እስከ ፡ ገጽ ፡ ..... ፴፪
፱ ፤ የአቶ ፡ ግዴለውና፡ የወይዘሪት፡ ቡርክት ፡ ጋብቻ፡
ከገጽ ፡ ፴፪ ፡ እስከ ፡ ገጽ ፡ .... ፴፫
፲ ፤ መደምደሚያው ፡ ከገጽ ፡ ፴፫ ፡ .... ፴፩

— መቅድም ። —

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሰብኩት ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ መጻሕፍቶችን ፡ ሳነብ ፡ ደራሲዎች ፡ በብዙ ፡ ትጋት ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ተረዳሁ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እኔም ፡ ለመጻፍ ፡ ሞከርኩ ። በየዕለቱም ፡ የምጽፋቸው ፡ ቃላት ፡ በቀን፡ ብዛት፡ ስለ ፡ ተጠራቀሙልኝ ፡ ጥሩ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲሆንልኝ፡ ከቀን ፡ ወደ፡ቀን፡ ከ፲፬፻፺፪ ፡ ወደ ፡ ፲፬፻፺፫ ፡ ከ፻፫ ፡ ወደ ፡ ፻፭ ፡ ከ፻፭ ፡ ወደ ፡ ፻፮ ፡ እያጣራሁ ፡ እጽፍ ፡ ጀመር ። ጅምሬንም ፡ ፈጸምኩ ።

ሐሳቡን ፡ እያነቃሁ ፡ የጻፍኩትም ፡ ሌሊት ፡ ሌሊት፡ ከእንቅልፌ ፡ ስነቃ ፡ ብዙ ፡ ሐሳብ ፡ ስለሚገለጥልኝ ፡ ደብተርና ፡ ብዕሬን ፡ እራስጌዬ ፡ እያስቀመጥኩ ፡ እተኛለሁ ።

ከእንቅልፌም፡ በምነቃበት፡ ሰዓት ፡ ትዝ ፡ የሚለኝን፡ ሁኔታ ፡ ወዲያውኑ ፡ እጽፋለሁ ። ቀንም፡ በትምህርት፡ቤት፡ በዕረፍት ፡ ጊዜዬ ፡ በየአትክልቱና ፡ በየአበባው ፡ ውስጥ ፡ እተዘዋወራለሁ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ሲገልጥልኝ ፡ እጽፋለሁ ።

ይህን ፡ ድርሰቴን ፡ አባቴ ፡ አሳትምልሃለሁ፡ ስላሉኝ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለኝ ፤ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ሐሳቤን ፡ እያስፋፋሁ ፡ ጻፍኩ ።

— መግቢያ ። —

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የተነገረው ፡ አብዛኛው፡ እንዳንድ ፡ ምሳሌ ፡ የያዘ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ በመጠኑ ፡ ለቲያት ርም ፡ ትርዕይት ፡ እንዲሆን ፡ በማለት ፡ በግጥም ፡ መልክ ፡ በ፲፱፻፺፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተዘጋጀ ።




ጽሑፍህን ፥ አሳትምልሃለሁ፥ በርትተህ ፥ ተማር ፥ ስላ
ሉኝ ፥ ለውድ ፥ አባቴ ፥ ያቀረብኩት ፥ ምሥጋና ፤

ውድ ፥ አበባ ፥ ሆይ ፤

ውድ ፥ አባቴ ፥ ሆይ ፤
ሰላምታ ፥ አቀርባለሁ ፥ በግጥም ፥ መሳይ፥
አልብሰው ፤ አስጊጠው ፥ አሳድገውኝ ፥
በትምህርት ፥ ገበታ ፥ አስቀምጠውኝ ፥
በሥነ ፥ ሥርዐት ፥ አስተምረውኝ ፥
መጽሐፍ ፥ እንድጽፍ ፥ ደብተር ፥ ገዙልኝ ፥
ይህን ፥ ድርሰት ፥ ስጽፍ፥ እጅግ ፥ ደስ፥አለኝ ፥
ረቂቁን ፥ ፈጸምኩ ፥ እግዚአብሔር ፥ ይስጥልኝ ፥
የሰጡኝን ፥ ተስፋ ፥ አስታውሳለሁኝ ፤
እባክዎ ፥ አባቴ ፥ ያሳትሙልኝ ።
በጠራ ፥ አማርኛ፥ ባልጽፈው ፥ በቅኔ ፥
በሕፃን ፥ አእምሮዬ ፥ ደረስኩት ፥ እንዳቅሜ ።
በድርሰት ፥ ላይ ፥ ስላለኝ ፥ ስሜት ፥ ለማበረታታት ፥
ሲሉ ፥ ውድ ፥ አባቴ ፥ ይህን ፥ መጽሐፍ ፥ አሳተሙልኝ ።
ይህም ፥ መጽሐፍ ፥ ስለታተመልኝ ፥ እጅግ ፥ ደስ ፥ አለኝ ።
ውድ ፥ አባቴንም ፥ ቀጥሎ ፥ በተመለከተው ፥ ግጥም ፥ አሞ
ገስኳቸው ።

— መግለጫ —

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ስላሳተሙልኝ ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁኝ ፤
ደግሞም ፡ በበለጠ ፡ የማስበው ፡ እኔ ፤
ትምህርት ፡ ለመፈጸም ፡ ነው ፡
በሕልሜም ፡ በውኔ ።
አባቴን ፡ እናቴን ፡ አስደስታለሁ ፡
በትጋት ፡ ተምሬ - እመረቃለሁ ።
ይህንን ፡ ምኞቴን ፡ አምላክ ፡ ፈጽምልኝ ፤
አባትና ፡ እናቴ ፡ እንዲደሰቱልኝ ፤
እግዚአብሔር ፡ በውነቱ ፡ ስለ ፡ ለገሠልኝ ፤
ለጥበብ ፡ እርምጃ ፡ ዕድል ፡ አገኘሁኝ ።



ክፍል ፡ ፩ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

አቶ ፡ ጋሜና ፡ ወይዘሮ ፡ ነቃሽ ።

አገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ካሏት ፡ ሰፋፊና ፡ ለምለም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶቿ ፡ አንዱ ፡ ጂማ ፡ ነው ። ጂማ ፡ ለምለም ፡ አገር ፡ እንደመሆኑ ፡ ቡና ፡ በሰፊው ፡ ይገኝበታል ። በዚሁ አገር ፡ አቶ ፡ ጋሜ ፡ ገበሬ ፡ ናቸው ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ሰፊ የቡና ፡ ንግድ ፡ አላቸው ። አቶ ፡ ጋሜ ፡ ወይዘሮ ፡ ነቃሽ ፡ የተባሉ ፡ እንደስማቸው ፡ የነቁ ፡ ሳተና ፡ ሚስት ፡ አሉዋ ቸው ። አቶ ፡ ጋሜና ፡ ወይዘሮ ፡ ነቃሽ፡ በፍቅር ፡ የተሳሰሩ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ናቸው ። እንኳን ፡ ሌላ ፡ ቀርቶ ፡ አቶ ፡ ጋሜ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ በሄዱበት ፡ ወይም ፡ በሚሄዱበት ፡ ሰዓት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይነፋፈቃሉ ። ይኸውላችሁ ፡ በእንደዚህ ፡ ዐይነት ፡ አኳኋን ፡ አብረው ፡ ሲኖሩ ፡ ባልታ ሰበ ፡ ጥቂት ፡ ነገር ፡ ለመለያየት፡ ደረሱ ። ወይዘሮ ፡ ነቃሽ፤ የሴት ፡ ቆፍጣና ፡ ስለ፡ነበሩ ፤ ቤታቸውን፡ ሠርተው ፡ ቁብ። አሉ ።

ከጥቂትም ፡ ቀናት፡ በኋላ ፡ የወይዘሮ ፡ ነቃሽ ፡ እናት፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ስለ፡ተለዩ፡ ወይዘሮ ፡ ነቃሽ ፡ በጎ ዘን ፡ ተውጠው ፡ የእናታቸውን ፡ ፍቅር ፡ በሚከተለው ፡ የጎዘን ፡ እንጉርጉሮዋቸው ፡ ገለጹ ።

እማምዬ ፡ እማምዬ ፤
ፍቅሬነሽ ፡ ፍቅርዬ ፡
በጣም ፡ አድርጌ ፡ አዘንኩልሽ ፡
ንብረትሽን ፡ ሁሉ ፡ ልውረስልሽ ፡
እንግዲህ ፡ አንቺ ፡ አትመለሽ ፡
በሕይወት ፡ ሳለሽ ፡ ደግ ፡ ነበርሽ ፡
ውረሽኝ ፡ ብለሽ ፡ ተናዘሽልኝ ፡
ነቃኺ፡ ልጅሽ፡ ልረከበው፡ ነኝ ። ካሉ፡ በኋላ ፡ በዚሁ፡ ልቅሶ ፡ ላይ ፡ ከሩቅ ፡ አቶ ፡ ጋሜን ፡ ያዩዋቸዋል ። በመና ደድ ፡ እንጉርጉሮዋቸውን ፡ አከታትለው ፡ እንዲህ፡ አሉ።
«ብዙ ፡ ጊዜሽ ፡ ነው ፡ አንቺ ፡ ከታመምሽ»፡
የድሮ ፡ ባሌ ፡ ከቶ ፡ አልጠየቁሽ ፤
ፈታኝት ፡ ብለው ፡ እዚያው ፡ ቀሩልሽ ፡
መሞትሽን ፡ ሰምተው ፡ አሁን ፡ መጡልሽ ፤
ቤት ፡ አስከባሪ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ የለሽ ።
ስለ ፡ አንቺ ፡ መሞት ፡ አላዘኑም ፡
ተቅበዝብዘዋል ፡ አቶ ፡ ጋሜም ።
ስለኑዛዜው ፡ ጠይቀውኛል ፡
መሬት ፡ ለመውሰድ ፡ አሰፍስፈዋል ።
ወይ ፡ አቶ ፡ ጋሜ ፡ ይሙቱልሽ ፡
ከነጋሜያቸው ፡ ይፍረሱልሽ ፡
ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ምንም ፡ አይጠቅሙሽ ።

ብትታመሚ ፡ ከኖ ፡ አልጠየቁሽ ፡
አንቺ ፡ ስትሞቺ ፡ አላዘኑልሽ ፡
መሬት ፡ ለመውሰድ ፡ አሁን ፡ መጡልሽ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

አቶ ፡ ጋሜም ፡ የቀድሞ ፡ ባለቤታቸው ፡ የወይዘሮ ፡ ነቃሽ ፡ የጎዘን ፡ እንጉርጉሮ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ተና ደዱና ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ የጎዘን ፡ እንጉርጉሮ ፡ መልስ ፡ ሰጡ ።

የነቃሽ ፡ እናት ፡ ወደቱ ፡ ሂዱብኝ ፡ ንገሩኝ ፡
ሰዎች ፡
ልጃቸው ፡ ነቃሽ ፡ በጣም ፡ አዝናለች ፡
ሰዎች ፡ ብጠይቅ ፡ አሁን ፡ ነገሩኝ ፡
የነቃሽ ፡ እናት ፡ ሞተዋል ፡ አሉኝ ።
አማትዬ ፡ አማትይዬ ፡
ምን ፡ ሆነው ፡ ሞቱ ፡ ወይኔ ፡ እዬዬ ።
ታመው ፡ አልጠየኩ ፡ ማን ፡ ነገረኝ ፡
ጠርጥሬ ፡ መጣሁ ፡ እግር ፡ ጣለኝ ፡
ነቃሽም ፡ ብትሆን ፡ ከኖ ፡ አትነግረኝ ፡
በጥቂት ፡ ነገር ፡ ተለየችኝ ።
እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ልወርስዎ ፡ ነኝ ።
ወራሽ ፡ የለዎት ፡ መቼም ፡ እኔው ፡ ነኝ ።

ነቃሽ ፡ ልጅዎ ፡ ትከተልዎት ፡
ለብቻ ፡ አይሂዱ ፡ ልጅ ፡ እያለዎት ።
መሸኘቱንስ ፡ ማንም ፡ ይሸኛል ፡
ብቻ ፡ እንዳይሄዱ ፡ ሰው ፡ ያስፈልጋል ።
ስለ ፡ ሀብቱም ፡ እኔ ፡ አለዎት ፡
ሀብቱን ፡ እኔ ፡ ልያዝልዎት ፡
ማንም ፡ አይነካው ፡ ልጠብቅልዎት ።

የአቶ ፡ ጋሜን ፡ የጎዘን ፡ እንጉርጉሮ ፡ የሰማ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተላቀሰ ። ዕንባ ፡ በዕንባ ፡ ሆነ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ አልቃሽ ፡ ተነሥታ ፡ የጎዘን ፡ እንጉርጉሮዋን ፡ ቀጠለች ።

የነቃሽ ፡ እናት ፡ ደጎና ፡ ይሁኑ ፡
ከሸኘንዎት ፡ እዚያው ፡ ይሁኑ ።
ይህ ፡ አቶ ፡ ጋሜ ፡ ይከተልዎት ፡
ሊወርስ ፡ መጥቷል ፡ የርሶን ፡ መሬት ፡ በማለት ።

የጎዘን ፡ እንጉርጉሮዋን ፡ እንደ ፡ ፈጸመች ፡ ስለ ፡ ሀብቱ ፡ ክርክር ፡ ሌላ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ተመረጠ ። የተመረጠውም ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ሁሉን ፡ ለኔ ፡ የምትሉ ፡ ወደኔ ፡ ኑ ፡ ብሎ ፡ ጠራቸው ።

ጉዳዩንም ፡ ለማየት ፡ በአጠገቡ ፡ የተቀመጡትን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ትችት ፡ ጠየቀ ። ተቺዎቹም ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተውን ፡ ትችት ፡ ሰጡት ።

የሽማግሌዎች ፡ ትችት ።

ነቃሽና ፡ ጋሜ ፡ ለሀብት ፡ ጓጒተው ፤
ተጨቃጭቀው ፡ መጡ ፡ ቅድም ፡ ተካሰው ።
የሰው ፡ ሀብት ፡ ለመውሰድ ፡ ምነው ፡ አቶ ፡ ጋሜ ፡
ጭቅጭቅ ፡ አነሡ ፡ ያውም ፡ ለዚች ፡ ዕድሜ ።
ሀብት ፡ ከሚመኙ ፡ በጣሙን ፡ አርጅተው ፤
ከነቃሽ ፡ ጋር ፡ ታርቀው ፡
ብትቈርቡ ፡ ምነው ።
በመጨረሻውም ፡ ውሎ ፡ ላፈር ፡ ሲሆን ፤
የሰው ፡ ሀብት ፡ ፈለጉ ፡ ዘንግተው ፡ ይኸንን ።
ሽማግሌ ፡ ነዎት ፡ ይበልጣል ፡ የነፍሱ ፤
ጋብቻዎን ፡ ያጽኑ ፡ ነቃሽን ፡ መልሱ ።
ከነቃሽ ፡ ጋር ፡ ታርቀው ፡ ሀብቱን ፡ እንዲወርሱ ።
ጌታው ፡ አቶ ፡ ጋሜ ፡ ያዳምጡን ፡ በውነት ፤
ተጋብቶ ፡ መፋታት ፡ ኃጢአት ፡ ነው ፡ በውነት ፡
ከእንግዲህስ ፡ ወዲያ ፡ ዕርቁን ፡ አስቡበት ።
ከላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ትችት ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡
የዘመድ ፡ ዳኛው ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ፍርዱን ፡ ሰጠ ።

ፍ ር ድ ።

ሽማግሌው ፡ ጋሜ ፡ ልንገርህ ፡ በውነት ፡
ከሚስት ፡ አትጣላ ፡ በመሬት ፡ ሀብት ፤

ሀብቱ ፡ ያማትህ ፡ ነው ፡ የሚስትህ ፡ እናት ፡
ከቶ ፡ በምን ፡ ነገር ፡ አሰብህ ፡ ለመቀማት ።
ይልቁንስ ፡ ስማኝ ፡ አድምጥ ፡ የኔን ፡ ምክር ፡
ነቃሽን ፡ ታረቃት ፡ ስለኑሮህ ፡ ፍቅር ፤
ይቅር ፡ ለቤቱ ፡ በል ፡ ታገኛለህ ፡ ክብር ።
ከነቃሽ ፡ ጋር ፡ ስትሆን ፡ ሀብቷን ፡ ታገኛለህ ፡
አንድ ፡ ላይ ፡ ስትኖሩ ፡ ትበለጽጋለህ ።

«ውሎ ፡ ላፈር ፡ አይቀር ፡ ነፍስህ ፡ እንዲማር ፡
ቄርባችሁ ፡ ጸልዩ ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ።

አቶ ፡ ጋሜና ፡ ወይዘሮ ፡ ነቃሽ ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ ተጸጽተው ፡ ይቅር ፡ ለቤቱ ፡ ብለው ፡ ታረቁ ። የዘመድ ፡ ዳኛ ውና ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ባሉበት ፡ አዝማሪ ፡ ተጠርቶ ፡ አቶ ፡ ጋሜና ፡ ወይዘሮ ፡ ነቃሽ ፡ የደስታ ፡ ውዝዋዜ ፡ በዜማና ፡ በግጥም ፡ አሳዩ ። የደስታቸውም ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ በሽብሸባውና ፡ በዕልልታው ፡ ተቀበሏቸው ።

ከውዝዋዜውም ፡ በኋላ ፡ ዕረፍት፡ ሆነ ። ቀጥሎም፡ ምሳና ፡ መጠጥ ፡ ቀረበ ። ይህም ፡ ግብዣ፡ እንዳበቃ ፡ አቶ፡ ጋሜና ፡ ወይዘሮ ፡ ነቃሽ ፡ የደስታ ፡ ውዝዋዜያቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ወይዘሮ ፡ ነቃሽ ፡ ባለቤቴ ፡
ምክሬን ፡ ስሚ ፡ በሞቴ ።
እንቁጥል ፡ የበጎ ፡ ተግባር ፡

መፋቀርን ፡ እንማር ፡
ተግተን ፡ እንጸልይ ፡ ነፍሳችን ፡ እንዲማር ፡
በሥጋ ፡ ወደሙ ፡ ይገኛል ፡ ታላቅ ፡ ክብር ።
የጽድቅ ፡ መገኛ ፡ ንጹሕ ፡ ልብ ፡ ነው ፡ በውነት ፡
ልቡናችን ፡ ይብራ ፡ በትሕትና ፡ እንመሥርት ።
መድኃኒት ፡ ነውና ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡
ሥጋውን ፡ ወደሙን ፡ ለመቅመስ ፡ እንትጋ ።

ክፍል ፡ ፪ ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

አጩሌ ።

አጩሌ ፡ የሚባል ፡ ጮሌ ፡ በወር፡ አሥራ ፡ አምስት፡ ብር ፡ ደመወዝ ፡ አቶ ፡ እንደውነቱ ፡ ለሚባል ፡ ባላባት ፡ ተቀጠረ ። በዚህም ፡ ደመወዝ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሲያገለግል፡ ሞረ ። ለሌሎቹ ፡ ሠራተኞቹ ፡ የደመወዝ ፡ ጭማሪ ፡ ሲደ ፡ ረግ ፡ አጩሌ ፡ ሳይጨመርለት ፡ በመቅረቱ ፤ ይከነክነው ፡ ነበር ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የደመወዝ ፡ ጭማሪ ፡ እንዲ ደረግለት ፡ አቶ ፡ እንደውነቱን ፡ ጠየቃቸው ። የአምስት ፡ ብር ፡ ጭማሪ ፡ አደረጉለትና ፡ ደመወዙ ፡ በወር ፡ ሐያ ፡ ብር ፡ ሆነለት ። በዚህም ፡ ጥቂቶች ፡ ዘመናት ፡ አገለገለ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያገልግሎቱን ፡ ዘመን ፡ በመዘርዘር ፡ ታማኝ
ነቱን ፡ በመግለጽ ፡ ሽልማት ፡ እንዲሰጠው ፡ እያቅራራ ፡
ይፎክር ፡ ጀመር ። ይሽውም ፡ እንደሚቀጥለው ፡ ነው ።

ዘራፍ ፡ ዘራፍ ።

እኔ ፡ አጩላቸው ፡ የውነቱ ፡ አሸከር ፡
ጠላታቸውን ፡ የማበር ፡ እንደወጣ ፡ የማስቀር ፡
ጠላት ፡ ቢመጣ ፡ እጋፈጣለሁ ፡
በመሣሪያቸው ፡ አባርራለሁ ።
አንድም ፡ ሳያመልጥ ፡ እማርካለሁ ፡
ዘራፍ ፡ የእንደውነቱ ፡ አሸከር ፡
ቆሜያለሁ ፡ ከበር ፡
ማንም ፡ አይደፍራት ፡ የጌታዬን ፡ በር ፡
በጉብዝናዬ ፡ የምትከበር ።
አቶ ፡ እንደውነቱ ፡ ጠጅ ፡ ይጠጣሉ ፡ በብርሌ ፡
ያንቄረቀርራል ፡ አጩሌ ።
ምን ፡ አለባቸው ፡ እኔ ፡ ካለሁ ፡
ጠላታቸውን ፡ አባርራለሁ ።
እኔ ፡ አቶ ፡ አጩሌ ፡ በታማኝነት ፡
አገልግያለሁ ፡ አሥር ፡ ዓመታት ።
የኔ ፡ ጌታ ፡ እንደውነቱ ፡
ይሸልሙኛል ፡ ከሀብቱ ።

ስማቸውም ፡ እውነት ፡ ነው ፡
ይታዩኛል ፡ ተቀምጠው ፡
እወንበር ፡ ላይ ፡ ሆነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጌታውን ፡ ቢመለከት ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ያዩት ፡ ጀመር ። ቀጥሎም ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ አይ ሥቄ ፡ ወይም ፡ አይነጋገሩ ፤ ወይም ፡ አያመሰግኑኝ ፤ እንዲ ያውነዝም ፡ ብለው ፡ ይመለከቱኛል ። እኔስ ፡ ስለ፡ቆከራዬ ፡ ይሸልሙኛል ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ቢነግራቸው ፡ ፊታቸ ውን ፡ ፈገግ ፡ አሉና ፡ የለበሱትን ፡ ካባ ፡ ሸለሙት ። እርሳ ቸውም ፡ ይኸንን ፡ ዓለም ፡ በአላፊነቱ ፡ በመናቅ ፡ ወደማያ ልፈው ፡ መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ለመግባት ፡ በማሰብ ፡ መነኑ ። መመነናቸውን ፡ ግን ፡ አሸከራቸው ፡ አጩሌ ፡ ስለሚያውቅ ፡ ሞቱ ፡ ብሎ ፡ አስወራ ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

አጩሌም ፡ ብቻውን ፡ ያንጐራጕር ፡ ጀመር ።
አቶ ፡ እንደውነቱ ፡ ያገሬ ፡ ባላባት ፡
የተውትን ፡ ሀብት ፡ ልጠብቅልዎት ፡
በመብትዎ ፡ እኔ ፡ ልዘዝበት ፡
ወራሽ ፡ የሚሆን ፡ ልጅ ፡ የለዎት ።
ከዘመድ ፡ እኔ ፡ እሻላለሁ ፡
ለብዙ ፡ ዘመን ፡ አገልግያለሁ ።

ዐሥር ፡ ዓመታት ፡ አገልግዬ ፡
ካባ ፡ ሸለሙኝ ፡ ጌታዬ ።
ጌታዬ ፡ ሂዱ ፡ መነኑ ፡
ወረስኳቸው ፡ አሁኑኑ ።
በሰጡኝ ፡ ካባ ፡ አጌጥኩ ፡
በወንበራቸው ፡ ተቀመጥኩ ።
ካባው ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ የሸለሙኝ ፡
ባቶ ፡ እንደውነቱ ፡ ተመሰልኩኝ ።
በሰጡኝ ፡ ካባ ፡ ተጠቀምኩበት ፡
ሀብታቸውንም ፡ አገኘሁት ፡
በመብታቸውም ፡ ገባሁበት ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

የአቶ ፡ እንደውነቱ ፡ ዘመዶች ፡ ከያለበት ፡ ተሰብ ስበው ፡ ቢመጡ ፡ ካባ ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡ በወንበር ፡ ተቀ ምጠ ፡ አዩ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ የአጩሌና ፡ የአቶ ፡ እንደው ነቱ ፡ መልክ ፡ ተመሳሳይ ፡ ስለሆነ ፤ አልቃሽ ፡ ዘመዶች ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፤ ዘመዳችን ፡ እኛሁና ፡ በሕይወት ፡ አሉ ። ሞቱ ፡ ብለው ፡ የነገሩን ፡ ሰዎች ፡ ያሞታችን ፡ ተቃራኒ ፡ እንደሆኑ ፡ አይታወቅም ። እንዲያውም ፡ አስመስሎባቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይይላቸው ፡ በማለት ፡ እየተጸጸቱ እባላ

ባቱ ፡ መቀመጫ ፡ ፊት ፡ ተጠጉ ። እንደተጠጉም ፡ ቀጥሎ፡ በተመለከቱት ፡ ሰላምታ ፡ አቀረቡላቸው ።

ደኅና ፡ ይስጥልን ፡

አጐታችን ።

እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ዘመዶቼ ፡ ከወዴት ፡ መጣችሁ ?

ትናንት ፡ ተነሣን ፡ ልንጠይቅሁ ፡

ምን ፡ ሆኜ ፡ ነበር ፡ እባካችሁ ?

ትናንት ፡ አረዱን ፡ አቶ ፡ ይብረሁ ።

ሞቷል ፡ በማለት ፡ ነገራችሁ ?

ኧረ ፡ እናቶ ፡ ይብረሁ ፡ ዘሩት ፡ ወሬውን፡

እርስዎ ፡ ሙተው፡ አረዱን ፡ አሁን ።

ታዲያ ፡ መቼ ፡ ልትቀብሩኝ ፡ ነው ?

አጐታችን ፡ ሲሞቱ ፡ ነው ።

ሞቱንማ ፡ ሰምታችሁ ፡ የለምን ?

አዎን ፡ ሰምተን ፡ መጣን ።

ብንመጣ ፡ ግና ፡ አልሞቱም ፡ እርስዎ ።

ታዲያ ፡ ምን ፡ ልትሉ ፡ ነው ?

ረጅም ፡ ዕድሜ ፡ ይስጥዎ ።

እስቲበሉ ፡ በድድዎ ፡

ዘመዶቼ ፡ ምነው ።

በድድ ፡ ብላ ፡ ስድብ ፡ ነው ።
የለም ፡ በድድ ፡ ብላ ፡ ማለት ፡
ምርቃት ፡ ነው ፡ በውነት ።

አንደኛው ፡ ዘመድ ፡ አላስችል ፡ ብሎት ፡ ብድግ ። አለና ፡ አጐታችን ፡ እነኝህ ፡ አሁን ፡ የሚመርቁዎት ፡ ሁሉ፡ ትናንትና ፡ ሞትዎን ፡ ሰምተን ፡ ስንመጣ ፤ አንድም ፡ ያዘነ፡ የለም ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡ መንገድ ፡ ለመንገድ ፡ እየተ ጣላን ፡ ለገላጋይ ፡ ታክተን ፡ ነው ፡ እዬህ ፡ የደረስነው ።

እንዴት ፡ በል ? አገር ፡ ቤት ፡ ያለውን ፡ መቶ ። ጋሻ ፡ መሬት ፡ እነኝህ ፡ አራቱ ፡ ዘመዶችዎ ፡ ሊከፋፈሉ ፡ ወቅደው ፡ ይኸ ፡ ለኔ ፤ ይኸ ፡ ለኔ ፡ በማለት ፡ ተፋጅተው ፡ ያገር ፡ ሽማግሌ ፡ ገላግሎዋቸው ፡ ነው ፡ የመጡት ።

እንዴት ፡ ገላገሉዋቸው ? ላርባው ፡ በሽማግሌ ፡ ትከፋፈላላችሁ ። አሁን ፡ ግን ፡ ሂዳችሁ ፡ እርማችሁን ፡ አውጡ ፡ ብለውን ፡ መጣን ።

አወይ ፡ እነሱስ ፡ ያገር ፡ ቤቱን ፡ ተመኙ ፡ አንተሳ ?
እኔማ ፡ እዬሁ ፡ እከተማው ፡ ያለውን ፡ ነዋ !
ምንድነው ፡ በል ፡ እከተማ ፡ ያለው ?
ቤትዎን ፡ ንብረትዎን ፤ ልብስዎን ፤ ጌጥዎን ፡ መሣሪያዎን ፡ በሙሉ ፡ ነዋ !
ኧረ ፡ ብልጥ ፡ ነህ ፡ ጃል ? አዎን ፡ ጮሌ ፡ ነኝ ።
በሉ ፡ እንግዲህ ፡ እስክሞትላችሁ ፡ ጠብቁ ።

አዬ ፡ ልጅ ፡ ይወልዳሉዋ !

እንዴ ፡ ታዲያ ፡ አሁኑኑ ፡ ልትነጥቂኝ ፡ ነው ?

ኧረ ፡ ምን ፡ በወጣን ፡ አጐታችን ።

እርስዎ ፡ ደኅና ፡ ይሁኑልን ።

አጐታችን ፡ እንሰናበትዎት ፡

መሄዳችን ፡ ነው ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ቤት ፡ በማለት ፡ ተሰነባብተው ፡ ከተለያዩ ፡ በኋላ ፤ መለስ፡ ብለው ፡ ቀጥሎ፡ ያለውን ፡ ጥያቄ ፡ አቀረቡ ።

አጐታችን ፡ ለካስ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ረስተን ፡ ኖራል ?

ምንድነው ፡ በሉ ? ያ ፡ አጬሌ ፡ የሚባለው ፡ አሽከርዎ ፡ አለ ?

የለም ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ንቆ ፡ መንኗል ።

ደግ ፡ ደግ ፤ ምነዋ ? አዬ ፡ እኛ ፡ እሱን ፡ እንጠረጥረው ፡ ነበር ።

እንዴት ፡ እባካችሁ ?

አንድ ፡ ቀን ፡ እወርሳችኋለሁ ፡ እያለ ፡ ያወራ ፡ ነበር፡ አሉ ።

አዬ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ወሬ ፡ አትስሙ ፤ እኔ ፡ አጐታችሁ ፡ ብርቱ ፡ ነኝ ። እንዳላችሁትም ፡ አኳኋኑን ፡ ሳየው በል ፡ ስፍራህን ፡ ፈልግ ፡ በማለት ፡ አሰናበትኩት ። እርሱም ፡ በዚሁ ፡ ተመሮ ፡ መነነ ።

አዬ ፡ ጐልማሳ ፡ ነበር ። እንዴት ፡ መነነ ?
ስሙኝ ፡ ዘመዶቼ ፡

እንሰማለን ፤ እንደምታውቁት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የቀረበው ፡ ሕፃንም ፡ ሆነ ፡ ጐልማሳ ፡ ወይም ፡ ሽማግሌ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ንቆ ፡ ይመንናል ። አዎን ፡ ይህስ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ስሙ ፡ ልንገራችሁ ። ዘመዶቼ ፡

እሺ ፡ እንሰማለን ። ወደአገራችሁ ፡ ስትሄዱ ፡ ምናል ባት ፡ አጩሌን ፡ እገዳም ፡ ወይም ፡ እጫካ ፡ ቢያጋጥማችሁ ፡ እንዳትጠጉት ። አስመስሎ ፡ ያወራል ። ቢጠራችሁም ፡ እንቢ ፡ በሉት ። ይልቁንም ፡ እኔን ፡ ስለሚመስል ፡ እንዳ ያሳስታችሁ ።

እሺ ፡ አጐታችን ፡ አናስቀርበውም ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተሰነባብተው ፡ ተለያዩ ።

ምዕራፍ ፫ ።

አቶ ፡ እንደውነቱ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ አቶ ፡ አጩሌ ፡ በማጭበርበር ፡ ያቶ ፡ እንደውነቱን ፡ ሀብት ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ተጠቀሙበት ። ነገር ፡ ግን ፡ እርጅና ፡ ስለደረሰባቸው ፡ በሠሩት ፡ ተንኰል ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ አድር ገው ፡ ከመጸጸታቸው ፡ የተነሣ ፤ ድግስ ፡ ደግሰው ፡ ያገሬ ውን ፡ ሰው ፡ በሙሉ ፡ ጋበዙ ። በግብጥውም ፡ ወቅት ፡ አስ ቀድሞ ፡ በማጭበርበር ፡ ሠርተውት ፡ የነበረውን ፡ ጎጢ

አት ፡ እሰዎቹ ፡ ፊት ፡ ጮክ ፡ ብለው ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ለን
ስሓ ፡ አባታቸው ፡ ተናዘዙ ። ይኸውም፡ እንደሚቀጥለው፡
ነው ።

ስሙ ፡ ስሙ ፡ እኔ ፡ የአቶ ፡ እንደውነቱ ፡ አሽከር ፡
አጩሌ ፡ የምባለው ፡ ነኝ ፡ አቶ ፡ እንደውነቱ ፡ መንነዋል፤
እንደ፡መነኑም ፡ እኔ ፡ የሳቸውን ፡ ሀብት፡ በሙሉ፡ወረስኩ።
ነገር ፡ ግን ፡ ለቸርነቱ ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ አምላክ ፡ በሕይ
ወት ፡ እስካሁን ፡ አኖረኝ ። በፈጸምኩትም፡ ማጭበርበር ፡
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይጸጽተኝ ፡ ነበር ። ይኸንንም ፡ በማሰብ ፡ ከሀ
ብቱ ፡ ሲሶውን ፡ ለድኻ ፡ መጸወትኩ ። የአቶ ፡ እንደውነ
ቱንም ፡ ሀብት ፡ በማጭበርበር ፡ በመውሰዴ ፡ እግዚአብሔር፡
በሕልሜ ፡ ይገሥጸኝ ፡ ነበር ።

እንግዲህ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ያቶ ፡ እንደውነቱ ፡ ዘመ
ዶች ፡ ይህን ፡ ሀብት ፡ በሙሉ ፡ እንዲረከቡኝ ፡ ለምኑልኝ።
እባካችሁ ።

እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይለኝ ፡ ዘንድ ፡
ነፍሴንም ፡ ይምራት ፡ ዘንድ ፤

አቶ ፡ አጩሌ ፡ እጅግ ፡ ከመጸጸታቸው ፡ የተነሣ ፡
ኀዘናቸውን ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ እንጒርጒሮ፡ ገለጹ።

የኔ ፡ ሥራ ፡ እንዲያው ፡ በክፋት ፡
ከተላላኪነት ፡ ባላባትነት ፡
በማጭበርበር ፡ ነው ፡ በብልጠት ፡

የአቶ ፡ እንደውነቱን ፡ ሀብት ፡
ብዙ ፡ ዘመናት ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡
ፈነጨሁበት ፡ በውነት ፡
የባላባቱን ፡ ንብረት ።
ሠላሳ ፡ ዘመናት ፡ ተከበርኩበት ።
ጸጽቶኝ ፡ ነበር ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡
በሠራሁት ፡ ኀጢአት ።
በቃኝ ፡ ይቅርብኝ ፡ የሰው ፡ ሀብት ፡
ዘመዶቻቸው ፡ ይረከቡት ።
ወለዱን ፡ ጭምር ፡ እከፍላለሁ ፡
ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በልቻለሁ ፡
የግል ፡ ሀብቴን ፡ እሰጣለሁ ።
የሰማይ ፡ አባቴ ፡ እግዚአብሔር ፡
ማረኝ ፡ ጌታዬ ፡ ቅዱስ ፡ ቸር ፡
ውሎ ፡ ላፈር ፡ አይቅር ፡ ነፍሴ ፡ እንዲማር ።
ለቸርነትህ ፡ ወሰን ፡ የለህ ፡
ሁሉን ፡ ትታገሣለህ ።
የኔንም ፡ ክፋት ፡ ታገሥኸኝ ፡
ለንስሓ ፡ ሞት ፡ አበቃኸኝ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለአቶ ፡ እንደውነቱ ፡ ዘመዶች ፡ መሬቱን ፡ ሀብቱን፤ ከነወለዱ፡ ካስረከቡ፡ በኋላ ፤ የነፍሳቸውን ፡ ለማሳመር ፡ እርሳቸውም ፡ እንደጌታቸው ፡ መነኑ ።

ክፍል ፡ ፫ ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

«ወይዘሮ ፡ «ሁሉ ፡ አማረሽ፡ » የሚባሉ ፡ ቤተ፡ክርስ ቲያን ፡ ሳሚ ፡ «ብሬ ፡ የሚባለውን ፡ አሽከራቸውን ፡ አስከ ትለው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲሄዱ ፡ አሽከርዬው ፡ እኋላ ፡ እኋላ ፡ እየተከተለ ፡ ያፈዝባቸው ፡ ጀመር ። ይኸ ውም ፡ እንደሚቀጥለው ፡ ነው ።

እሜትዬ ፡ ላይዘልቅ ፡ ጸሎት ፡
እንዲያው ፡ ለቅሥፈት ፤
ጸሎት ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ አላወቁበት ።
ጸሎት ፡ መጸለይ ፡ ቀልድ ፡ መሰለዎ ፡
በየመንገዱ ፡ ሣቅ ፡ ማብዛትዎ ።
ታላቅ ፡ ነውር ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ማማት ፡
ጸሎተኛዋ ፡ እመቤት ፡
ሰው ፡ እንዳያሙ ፡ እባክዎት ፡
እሜትዬ ፡ እመቤቴ ፡ እንደዚህ ፡ ስልዎት ፡
ሀብቴ ፡ እንዳይቀነስ ፡ እባክዎት ።
እሜትዬ ፡ እመቤቴ ፡
ልንገርዎ ፡ በሞቴ ።
የልብ ፡ ክፉት ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡
ልብዎን ፡ ያንጹ ፡ ተግተው ።

ባፍ ፡ እየሣቁ ፡ ልብን ፡ ማጥቈር ፡
ያራርቃል ፡ ከእግዚአብሔር ።
እመቤት ፤ — ምን ፡ አልክ ፡ አንት ፡
ባለጌ ፡ ነህ ፡ በውነት ፡
አሳዳጊ ፡ የበደለህ ፡
አባልጎ ፡ ያሳደገህ ፡
አስተዳደግ ፡ የጐደለህ ፡
ትሰድበኝ ፡ እንዲህ ፡ ደፍረህ ።
አሽከር ፤— ኧረ ፡ እሜቴ ፡
እመቤቴ ፡
አልሰደብኩዎትም ፡ እናቴ ፡
እሜትዬ ፡ እመቤቴ ፡
ማርና ፡ ወተቴ ።
ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መቅረት ፡
አይገባም ፡ ላሮጊት ፡
እንዳይደርስብዎ ፡ ቅሥፈት ።
ጸሎትን ፡ አያስተጓጒሉ ፡
ማለድ ፡ ብለው ፡ ቡና ፡ አይበሉ ።
እመቤቴ ፡ ልንገርዎት ፡
የጎጢአት፡መሠረት፡ ታላቅ፡በደል፡ነው፡ሐሜት።
የሐሜተኛ ፡ ጸሎት ፡
አይሠምርለትም ፡ በውነት ።

እመቤት ፤—ምናልክ ፡ ብሩ ፡
ትፎክራለህ ፡ በየበሩ ፡ (በደስታ) ፡
ፉከራህ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡
ከመንገዱ ፡ ላይ ፡ አቆመኝ ፡
ከምሄድበት ፡ አስቀረኝ ።
ብሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፉከራህን ፡
ረሳሁት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡
ቅዳሴውም ፡ አልፉል ፡ መቼም ፡ አልደርስ ፡
ወደ ፡ ቡናዬ ፡ ልመለስ ።
አሽከር ፤— እመቤቴ ፡ እሜትዬ ፡
ቃሌን ፡ ያድምጡ ፡ እናትዬ ።
አሽከር ፡ ነህ ፡ ብለው ፡ አይንቀፉኝ ፡
ድኻ ፡ ነህ ፡ ብለው ፡ አይናቁኝ ፡
እኔም ፡ እንደርሶ ፡ ሰው ፡ ነኝ ።
ከመንፈሳዊ ፡ በተማርኩት ፡
ልምከርዎት ፡ በውነት ፡
ይድረስዎት ፡ በረከት ።
ውሎ ፡ ላፈር ፡ ነው ፡ መጨረሻው ፡
በበጎ ፡ መንገድ ፡ መመራት ፡ ነው ።

ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወይዘሮ ፡ ሁሉ ፡ አማረሽ ፡ የብሬ ፡ ምክር ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ ተረድተው ፡ የነፍሴን ፡ መን

ገድ ፡ ላሳምር ፡ በማለት ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ሄደው ፡ መነኰሱ። ከመነኰሱም ፡ ዕለት ፡ ጀምሮ ፡ ስሜ ፡ «ሁሉ ፡ አማረሽ ፡ » መባሉ ፡ ቀርቶ ፡ የነፍሴን ፡ ያዝኩት ፡ በሚባል ፡ ስም ፡ ልጠራ ፡ በማለት ፡ አስታወቁ።ከዚያችም ፡ ዕለት ፡ ጀምሮ ፡ ስማቸው ፡ እማሆይ ፡ የነፍሴን ፡ ያዝኩት ፡ ተባለ ።

ክፍል ፡ ፬ ።

ምዕራፍ ፲ ።

ሣቅህን ፡ ለነገ ።

ሣቅህን ፡ ለነገ ፡ አድርገው ።

ግድ ፡ የለው ፡ የሚባል ፡ ተማሪ ፡ በስንፍና ፡ የተ መሰጠ ፡ ትምህርት ፡ የሚጠላ ፡ ሣቅ ፡ የሚያበዛ ፡ ወሬኛ ፡ የሆነ ፡ ልጅ ፡ ነበር ።

ጓደኞቹ ፡ እነኅሩይ ፡ እነተዐውቀ ፡ ትምህርታቸውን ፡ እየፈጸሙ ፡ እንደየዕውቀታቸው ፡ ደረጃ ፡ (ዲግሪ) ፡ ከዩኒቨ ርሲቲው ፡ ቻንስለር ፡ እየተቀበሉ ፡ ወደየተግባራቸው ፡ ሲሰማሩ ፡ ግዴለው ፡ ገና ፡ በሣቅ ፡ ላይ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ የበጎ ፡ ተግባር ፡ የታማይገባው ፡ ቢሆንም ፡ እናትና ፡ አባቱ ፡ እየመከሩና ፡ እየገሠጹ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከመላክ ፡ አልቦዘኑም ። ምን ፡ ይሆናል ፡ ግዴለው ፡ ግዴለሽ ፡ ሆነና ፡ እንቢ ፡ አለ ። በዚህ ፡ ዐይነት ፡ እያስቸ ገረ ፡ ስድስት ፡ ዓመታት ፡ ኖረ ። በየዘመኑም ፡ ከፈተና ።

ስለማያልፍ ፡ አስተማሪው ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ጥያቄ ፡ አደረጉለት ።

መምህር ፡ ግዴለው ፡ ተግተህ ፡ ባለመማርህ ፡
ከፈተና ፡ ወደቅህ ፡
ብታውቀው ፡ ብትገነዘበው ፡
ይህ ፡ ታላቅ ፡ ጎፍረት ፡ ነው ።
የምትሰጠው ፡ መልስ ፡ ሲጠይቁህ ፡
ከአገባብ ፡ ውጭ ፡ ነው ፡ እባክህ ፡
ከዚህ ፡ በላይ ፡ ሣቅህ ፡
የሚደንቅ ፡ ነው ፡ ልንገርህ ፡
ለወደፊቱ ፡ በክፍልህ ፡
እንዳትሥቅ ፡ እባክህ ።
ግዴለው ፤ አስተማሪዬ ፡
መምህርዬ ፡
እንዳልሥቅማ ፡ ከተቈጡኝ ፡
ከት ፡ ብዬ ፡ ልሥቅ ፡ ነኝ ፡
ንግግርዎ ፡ ገረመኝ ፡
እንዳትስቅ ፡ ሲሉኝ ።
እያስመሰልኩ ፡ ካላወራሁ ፡
ጮክ ፡ ብዬ ፡ ካለፈለፍሁ ፡
ታዲያ ፡ ምን ፡ እባላለሁ ።
መሣቅማ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡

ተማር ፡ ሲሉኝ ፡ ይከፋኛል ።
አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ተማር ፡ ካሉኝ ፡
ወደዙረት ፡ መሄዴ ፡ ነኝ ።
ደጎና ፡ ይዋሉ ፡ መምህር ፡
እንዳይቄጡ ፡ በቁም ፡ ነገር ።
ወደሻዬ ፡ ቤት ፡ እስክደርስ ፡
መንደርደሬ ፡ ነው ፡ በሣቅ ፡ ፈረስ ።
ከዚያም ፡ ስመለስ ፡ እዳንስ ፡ ቤት ፡
አዬ ፡ ሙዚቃው ፡ ሲያስደስት ።
ልንገርዎ ፡ ታሪኬን ፡
የሆንኩትን ፡ አንድ ፡ ቀን ።
ሙዚቃው ፡ ገና ፡ ሲጀምር ፡
ከበራፉ ፡ ላይ ፡ ቆሜ ፡ ነበር ።
ጮክ ፡ ብሎ ፡ ቢያጓራ ፡
ጀመርኩልዎ ፡ ፉከራ ።
እንደ ፡ ፌንጣ ፡ እየዘለልኩ ፡
ቲፕ ፡ ታፕ ፡ ረገጥኩ ።
በሕይወቴ ፡ የሚለኝ ፡ ደስ ፡
በያለበት ፡ ስደንስ ።
ቴክሳስ ፡ ከሚባል ፡ ሻይ ፡ ቤት ፡
እጨፍራለሁ ፡ ያለ ፡ ዕረፍት ።
ያስደስታል ፡ የዳንሱ ፡ ቤት ፡

ተኳኩሎ ፡ በቀለማት ።
መብራቶችም ፡ ማማራቸው ፡
ጎብረ ፡ ቀለማት ፡ ናቸው ።
ከመንገዱ ፡ ዳር ፡ እንደ፡ሆንኩ ፡
የቡጊ ፡ ቡጊ ፡ ጮቤ ፡ ዘለልኩ ፡
ዝላዬንም ፡ እንደፈጸምኩ ፡
ወደ ፡ ቤቴ ፡ ተመለስኩ ፡
እያኝጨሁም ፡ ደረስኩ ።
እቤቴም ፡ ስገባ ፡ ሞቅ ፡ ብሎኝ ፡
ጭፈራው ፡ አቅበዘበዘኝ ፡
ጎረቤቶቼም ፡ ገሠጹኝ ፡
አታኝጭ ፡ ብለው ፡ ተቆጡኝ ፡
ብልግናህን ፡ ተው ፡ አሉኝ ።
ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ሣቅሁባቸው ፡
በጣም ፡ ቢገርመኝ ፡ ፈዛቸው ፡
ጨዋታው ፡ አልገባቸው ፡
ዳንስ ፡ መጨፈር ፡ አቃታቸው ።
ሞኞች ፡ ናቸው ፡ በውን ፡
አታኝጭ ፡ አሉኝ ፡ እኔን ።
ቢፈልጉማ ፡ መከበር ፡
ይጠይቁኝ ፡ ነበር ፡ መጨፈር ።
አስተማሪዬ ፡ በውን ፡

ቢሞክሩት ፡ ዳንሱን ፡
አይለዩም ፡ ነበር ፡ አንድ ፡ ቀን ።

ግዴለው ፡ እንደዚህ ፡ በመባለጉ ፡ አስተማሪው ፡ በጣም ፡ አድርገው ፡ ከማዘናቸው ፡ የተነሣ፡ ምክራቸውን፡ በመቀጠል ፡ እንዲህ ፡ አሉት ። ልጄ ፡ ሆይ ፡ ግዴለው ! ስማኝ ፡ እስቲ ፡ አድምጠኝ ፡ ልንገርህ ፡ በቁም ፡ ነገርም ፡ ምክሬን ፡ ተቀበል ፤ በዝርዝር ፡ ስነግርህ ፡ ይግባህ ። ይኸ ውም ፡ ከጓደኞችህ፡ ከነጎሩይና፡ ከነተአውቀ፡ ጋራ ፡ ሥስታ ችሁ ፡ አንድነት ፡ ፊደል ፡ ቈጥራችሁ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን፡ እነሱ ፡ አንተን ፡ አልፈው ፡ የደረሱበትን ፡ ታውቃለህ ።

ግዴለው ፡— አዎን ፡ አውቃለሁ ፤

መምህር ፡— በል ፡ ካወክ ፡ ንገረኝ ?

ግዴለው ፡— እቤታቸው ፡ ደረሱ ።

መምህር ፡— አንተ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ቀልድህን ፡ ተወኝ ፡ ብዬሃለሁ ።

ግዴለው ፡— ምን ፡ አደረግሁ ፡ ለተጠየቅሁት ፡ መልሱ ፡ ይህ ፡ በመሆኑ ፡ ነዋ !

መምህር ፡— እኔ ፡ የጠየቅሁህ፡ የትምህርታቸውን፡መጠን፡ ነው ፤ አንተን ፡ አልፈው ፡ እምን ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ እንድታስረዳኝ ፡ ነው ።

ግዴለው ፡—አስተማሪዬ ፡ ሆይ ፡ በትምህርት ፡ ከኔ ፡ ምን፡ ያህል ፡ ብልጫ ፡ እንዳላቸው ፡ ማወቅ ፡ የመ

ምህር ፡ ፈንታ ፡ ነው ። የደረሱበትን ፡ ለማ
የት ፡ ደግሞ ፡ ድርሰታቸውን ፡ ባለማንበቤ ፡
ላስረዳ ፡ አልቻልኩም ።

መምህር ፡— ኧረ ፡ ተው ፡ አትቀልድብኝ ፡ እባክህ ? በደ
ንቡ ፡ ተናገር ።

ግዴለው ፡— መምህሬ ፡ ሆይ ! ምን ፡ አጠፋሁ፡ እስካሁን፡
በደንብ ፡ ነው ፡ የምናገረው ። ባነጋገር ፡
የተዛነፍኩ ፡ አይመስለኝም ። እኔን፡ ከጠሉ፡
ንግግሬ ፡ ባይጥምዎት፡ ይሆናል ። ቢሆንም፡
እንደገና ፡ ላስረዳዎ ። « ጎሩይና ፡ ተአወቀ ፡
ወረቀት ፡ በመጻፍ ፡ በማንበብም ፡ ጐብዘ
ዋል ። ከተማሩትም ፡ በላይ ፡ በተፈጥሮ ፡
ዕውቀታቸው ፡ አዳዲስ፡ ሐሳብ ፡ እያመነጩ፡
መጻሕፍት ፡ ደርሰዋል፡ ይባላል ። እኔ ፡ ግን፡
አላነበብኩላቸውም ። ታዲያ ፡ እንደኔ፡የሚ
ደንሱ ፡ ይመስልዎታል ?

መምህር ፡— አዬ ፡ ግዴለው ፡ ተው ፡ ስማኝ ፡ አድምጠኝ!

ግዴለው ፡— እንዴ ፡ ቱው ፡ ካሉኝማ ፡ ምኑን ፡ ሰማሁት ፡
እንዲያው ፡ ዝም ፡ ነዋ !

መምህር ፡— ግዴለው ፡ አታፈዝብኝ ፡ አድምጠኝ ።አየህ፡
አሁን ፡ ልጅ ፡ በመሆንህ ፡ ትምህርት ፡

ጥቅም ፡ የማይሰጥ ፡ ይመስልሃል ፡ ቢገባህ ፡ መልካም ፡ ነበር ።

ግዴለው ፡— መምህሬ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ እኮ ፡ ደኅና ፡ ጐረምሳ ነኝ ፡ ለምንድነው ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡ ያሉኝ ?

መምህር ፡— አዬ ፡ ሰውነትህማ ፡ ጐርምሷል ፤ ከጉርምስ ናም ፡ ተላልፎታል ። በትምህርት ፡ ግን፡ገና፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ ነህ ።

ግዴለው ፡— መምህሬ፡ ሆይ፡ ይስሙኝ! ጎሩይ፡ ተአውቀን፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ይበልጠዋል ። ተአወቀ ፡ እኔን ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ይበልጠኛል ። በዕድሜስ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አንበላለጥም።እኩዮች ፡ ነን ። እንደሚያውቁት ፡ የሁለትና ፡ የሦስት ፡ ዓመታት ፡ ልዩነት ፡ እንደ፡ልጅና ፡ እንደ ፡ ዐዋቂ ፡ የሚያስቈጥር ፡ አይመስለኝም ። እነርሱም ፡ በትምህርት ፡ ቢበልጡኝ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ አይወዳደሩኝም ። ይኸውም እኔ ፡ በዳንስ ፡ በሣቅ ፤ በጨዋታ ፡ እበልጣቸዋለሁ ። ለመቼውም ፡ ቢሆን ፡ አይስተካከሉኝም ።

አስተማሪ ፡— ግዴለው ፡ የትምህርትን ፡ ጥቅም ፡ ለይተህ፡ ባለማወቅህ ፡ እኮ ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ የባለግኸው ። ይህ ፡ የሚገባህ ፡ ከዕድሜ ፡ ፫፬ ፡ ስታ

ደርግና ፡ ስትጐለምስ ፡ ነው።አሁን ፡ ምንም፡ ሊገባህ ፡ ባለመቻሉ ፡ አንተን ፡ መምክር ፡ እንዲያው ፡ መድረቅ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነብኝ ፡ የምሰጥህን ፡ ምክር ፡ ልገታ ፡ ነው ።

ግደለው ፡— መምህሬ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ በዕድሜ፡ ስጐለምስ፡ ሣቄን ፡ ልፍለፋዬን ፡ ወሬዬን ፡ ዳንሴን ፡ ዘፈኔን ፡ በበለጠ ፡ እያሻሻልኩ ፡ እጐለምሰዋለሁ ። ተዐውቀና ፡ ጎሩይ ፡ ሲጐለምሱ ፡ ትምህርታቸው ፡ ያረጅባቸዋል ፡ እንጂ ፡ መሻሻል፡ ሊያደርጉ ፡ የሚችሉ ፡ አይመስለኝም ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ እንደኔ ፡ ለመደነስ ፡ ቢፈልጉ ፡ ሰውነታቸው ፡ አይታዘዝላቸውም ። የኔም ፡ ዳንስ ፡ የሚወደደው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ነው።

መምህር ፡— በል ፡ ግደለው ፡ አንተ ፡ ምክሬን ፡ የማትቀበል ፡ ሞገደኛ ፡ ስለሆንክ ፡ ወጊድ ፡ ከፊቴ ፡ ዳግመኛ ፡ እዚህ ፡ ት/ቤት ፡ እንዳትመጣ ።

ግደለው ፡— ምነው ፡ መምህሬ ፡ ሞገደኛ ፡ ብለው ፡ ይሰድቡኛል ? በየትኛው ፡ መርከብ፡ ሲሄዱ ፡ ነው፡ እኔ ፡ ሞገድ ፡ ሁኜ፡ያሠቃየሁዎ ! እኔ ፡ በማውቀውና ፡ በተረዳሁት ፡ ሞገድ ፡ ማለት ፡ በውቅያኖስ ፡ አላስኬድ ፡ እያለ ፡ የሚያውክ፡ማዕ

በል ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ከርስዎ ፡ ጋራ ፡ የሚያ
ወራ ፡ አይደለም ፤ ለካስ ፡ ይሳሳታሉና !

አስተማሪ ፡— አንተ ፡ ደፋር ፡ ባለጌ ፡ በል ፡ ሂድ ፤

ግዴለው ፡— መምህር ፡ ሆይ ፡ ስለምን ፡ ተማሪዎቹን ፡
ይበድሉዋቸዋል ?

አስተማሪ ፡— እንዴት ፡ እባክህ ?

ግዴለው ፡— በዕረፍት ፡ ሰዓት ፡ እኮ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ እያሣሣቅ
ሁና ፡ እየዘፈንኩ ፤ እያኝጨሁ ፡ የማጫውታ
ቸው ።

አስተማሪ ፡— ግዴለው ፡ ያንተ ፡ መባለግ ፡ አንሶ ፡ እነሱ
ንም ፡ ታሳሥቅ ፡ ኖሩዋል ፡ ለካ ! በል ፡ አሁ
ኑኑ ፡ ሂድልኝ ፡ ወዲያ ።

ግዴለው ፡— አስተማሪዬ፡ ሆይ ! እስከዚህ፡ ምርር፡ብለው፡
ተቈጥተው ፡ የሚያባርሩኝ፡ ከሆነማ ፡ ከዛሬ፡
ጀምሮ ፡ ምክርዎን ፡ ተቀብያለሁ ። እሚያ
ዙኝን ፡ ሁሉ ፡ እፈጽማለሁ ። ትምህርቴን ፡
እቀጥላለሁ ፡ ይፍቀዱልኝ ፡ እባክዎ ?

አስተማሪ ፡— በል ፡ ምክሬን ፡ ከተቀበልህ ፡ ቀጥ ፡ ብለህ፡
ተግተህ ፡ ተማር ።

ግዴለው ፡ — እሺ ፡ መምህሬ ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ በርትቼ ፡
እማራለሁ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግዴለው ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ተግቶ፡በመ
ማር ፡ ዲግሪ ፡ ተቀበለ ። ከዕውቀቱም ፡ በላይ ፡ ትሕትና ፡
የተመላው ፡ ሆነና ፡ በቤተ ፡ ሰቦቹ ፤ በጓደኞቹ ፡ ዘንድ ፡
እጅግ ፡ ተወዳጅ ፡ ሆነ ። የትምህርቱን ፡ ጥቅም ፡ ከተረዳ ፡
በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተውን ፡ እያንገራገረ ፡ አባት ፡
እናቱን ፡ አስተማሪውን ፡ አሞገሰ ።

መከሩኝ ፡ እንድማር ፡
መልካሙ ፡ መምህር ፡
ተምሬ ፡ እኩል ፡ ሆንኩኝ ፡ ከጓደኞቼ ፡ ጋር ፡
ባጉል ፡ አነጋገር ፡
ሰውን ፡ እንዳልደፍር ፡
በበጎ ፡ አእምሮ ፡ ሰዎችን ፡ እንዳከብር ፡
በጣም ፡ አስተማሩኝ ፡ የትሕትና ፡ መምህር ።
በቀና ፡ ሕሊና ፡ አርቄ ፡ አያለሁ ፡
በውነት ፡ ማስተዋል ፡ እመለከታለሁ ፡
በንጹሕ ፡ ልቡና ፡ ሰውን ፡ እወዳለሁ ፡
በታላቅ ፡ ትሕትና ፡ አከብራችኋለሁ ።
ለናት ፡ አባቴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡
ዕውቀት ፡ ይቅባህ ፡ ብለው ፡ ባጣሙን ፡ ገሠጹኝ፤
ተማር ፡ ተማር ፡ ብለው ፡ ያለመሰልቸት ፡
ለዚህ ፡ አደረሱኝ ፡ ለታላቅ ፡ ዕውቀት ።
ከራሴም ፡ አብልጬ ፡ እወዳችኋለሁ ፡

እናትና ፡ አባቴ ፡ እጦራችኋለሁ ፡
ከበጎ ፡ አስተማሪ ፡ ዕውቀት ፡ ገብይቻለሁ ፡
አብቤ ፡ አፈራለሁ ፡ ግዴለው ፡ ልጃችሁ ፡
የኔንም ፡ አበባ ፡ እንዲያሳያችሁ ፡
ጢትና ፡ ማታ ፡ እጸልያለሁ ፡
ቸር ፡ እግዚአብሔር ፡ በሕይወት ፡ ያኑራችሁ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግዴለው ፡ የሕይወት ፡ ጓደኛ ፡ የምት ሆን ፡ ሚስት ፡ አግብቼ ፡ ልጆች ፡ እንዳገኝና ፡ እናትና ፡ አባቴም ፡ የኔን ፡ አበባ ፡ አይተው ፡ እንዲደሰቱልኝ ፡ በማ ለት ፡ አሰበ ። አስቦም ፡ ምኞቱን ፡ ለናቱ ፡ ገለጸ ። እናቱም ፡ በጣም ፡ ተደስተው ፡ ከአባቱ ፡ ጋራ ፡ ተመካከሩና ፡ « ቡር ክት ፡ » የተባለችዋን ፡ አስተዳደጉዋ ፡ በሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሆነውን ፡ ዐይነ ፡ አፋር ፡ ልጃገረድ ፡ አጭተው ፡ በሥር ዐተ ፡ ተክሊል ፡ በሕግ ፡ አጋቧቸው ። ከተጋቡም ፡ በኋለ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ቄዩ ፡ ቡርክት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለ ደች ። ግዴለው ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ስለ ፡ተወለደለት ፡ ከአባት ፡ ከእናቱ ፡ ጋራ ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ ተደሰቱ ። የግዴለው ፡ አባት ፡ አቶ ፡ መስከረምና ፡ እናቱም ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበች ፡ የልጃቸውን ፡ አበባ ፡ በማየታቸው ፡ ለዚህ ፡ ዕድል ፡ ላበ ቃቸው ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄደው ፡ ጸሎት ፡ አደረሱ ። ከቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሲመለሱ ፡ ለደስታው ፡

መግለጫ ፡ ታላቅ ፡ ግብጣ ፡ አድርገው ፡ ዘመድ ፡ አዝማዳ ቸውን ፡ ጠርተው ፡ ጋበዙ ።

ሕፃኑንም ፡ «አበበልን ፡ » ብለው ፡ ሰየሙት ። የደስ ታውም ፡ ሁኔታ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ግጥም ፡ እየደ ረደሩ ፡ ያንጐራጕሩ ፡ ጀመር ።

ግዴለው ፡ መስከረም ፡
አበበልን ፡ ግሩም ፡
አበባው ፡ መስከረም ፡
ያስደስታል ፡ በጣም ።
የመስከረም ፡ ነፋስ ፡ ተወዳጅ ፡ ነው ፡ ለካ ፡
ዝናቡ ፡ ሄደና ፡ ልምላሜ ፡ ተተካ ።
ዛፉ ፡ ዕፀዋቱ ፡ ልምላሜው ፡ የሣሩ ፡
የመስከረም ፡ ወራት ፡ እጅግ ፡ አስደሳች ፡ ነሽ ፡
የውነቷ ፡ ቡርክት ፡ አበባ ፡ አየንብሽ ።

መ ደ ም ደ ሚ ያ ።

ክቡራን ፡ አንባብያን ፡ ሆይ ።

የኔ ፡ የደራሲው ፡ ዕድሜ ፡ ፲፫፡ ዓመት ፡ ነው ። በዚህ፡ ዕድሜው ፡ እንዴት ፡ ሊደርስ ፡ ቻለ ፡ የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ይኖር ፡ ይሆን ? በአእምሮ ፡ ብልኅ ፡ ከሆኑና ፡ የእግዚአ ብሔር ፡ እርዳታ ፡ ካልተለየ ፡ በሰውነት ፡ ሕፃንነት ፡ ምክ ንያት ፡ ወረቀት ፡ ለመጻፍ ፡ ችግር ፡ የማይገጥም ፡ መሆኑ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ስለሆነም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ መግቢያ ፡ እንደተነገረው ፡ ሐሳቡ ፡ በሙሉ ፡ የኔው ፡ ነው ። አጻጻፍንም ፡ በየአርእስቱ ፡ እየተነተንኩ ፡ በያግባቡ፡ የጻፍኩት ፡ ራሴ ፡ ነኝ። የፊደሎቹን ፡ አሰካክችና ፡ አቀማመጥ፡ ብቻ ፡ አቶ ፡ ሞገስ፡ ኪዳኔ፡ ስለአሳዩኝ ፡ በዚችው፡ መጽሐፌ፡ ሳላመሰግናቸው ፡ አላልፍም ።

ተፈጸመ ።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ ።